**አዲሱ የትምህርት አመት ወደ ታላቅ አጀማመር አመራ**

የ2014-2015 የትምህርት አመት፣ ታይቶ ለማይታወቅ የተማሪዎች ብዛት በሮቹን ሲከፍት፣ ሰኞ ኦገስት 25 ወደ ታላቅ አጀማመር አመራ። የዲስትሪክቱ 202 ት/ቤቶች ከ154,000 በላይ ተማሪዎች በዚህ አመት እንደሚከታተሉ ይጠበቃል፣ ይህም በ2,800 ተማሪዎች አካባቢ ከ2013-2014 እድገት አሳይቷል። ባለፉት አምስት አመታት የተማሪዎች ምዝገባ ከ10,000 በላይ አድጓል እናም በ2018-2019 የተማርዎች ቁጥር 159,000 እንደሚያልፍ ይጠበቃል። MCPS አዲሱን አመት ከ23 አዲስ ርእሰ መምህራን እና ከ800 በላይ የሚሆኑ አዲስ አስተማሪዎች ጋር እየጀመረው ነው።

MCPS በዚህ አመት ላፕቶፖችና ታብሌቶች በዲስትሪክት ከዳር እስከዳር በሚገኙ የመማርያ ክፍሎች በማስተዋወቅ አዲስ ቴክኖሎጂ ማነሳሻ እያስገባ ነው። መነሳሻው መሳርያዎችን/መገልገያዎችን—በተለይ ጉግል ክሮምቡኮች (Google Chromebooks)—በሁሉም የ3ኛ፣ 5ኛ፣ እና 6ኛ ክፍሎች፣ እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማህበራዊ ጥናት መማርያ ክፍሎች በዚህ አመት ያስቀምጣል። መሳርያዎች በዚህ የትምህርት አመት በሶስት ደረጃ ይሰራጫሉ፣ ተጨማሪ ክፍሎችና የትምህርት አርእስቶች በሚመጡት አመቶች ይጨመራሉ።

የመነሳሻው ግብ ማስተማርንና መማርን ለማበልፀግ እና ተማሪዎችን በትምህርታቸው እንዲጠመዱና ትምህርትን ግላዊ ለማድረግ ተጨማሪ እድሎችን ለመፍጠር ነው። በክላውድ-በተመሰረተ የመማርያ መድረክ በመጠቀም፣ ይህ ቴክኖሎጂ ተማሪዎችንና ሰራተኞችን "በማንኛውም ጊዜ-የትም ስፍራ" ለስራቸው መዳረሻ ይሰጣል። ይህ ፕሮግራም ባለፈው አመት በት/ቤቶች ሙከራ ተደርጎበት በመቶዎች የሚቆጠሩ የMCPS መምህራን በመሳርያዎች አጠቃቀም በመማርያ ክፍሎች በሰመር ወራት ሰልጥነዋል።

ወላጆችና ተማሪዎች የሚወዷቸውን ፎቶግራፎች የትምህርት መጀመሪያ ቀን ሰኞ እንዲያስገቡ ተጋብዘው ነበር። MCPS ከ100 በላይ ተቀብሏል፣ እነዚህን የመጀመርያ ቀን ፎቶዎች መደርደርያ (gallery) ለማየት [እዚህ ](#)ይችላሉ።

ሰኞ ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት፣ ኦገስት 23 ቀን በተካሄደው አመታዊ የMCPS ተመልሶ-ወደ-ት/ቤት በአል ከ5,000 በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ሮክቪል የሚገኘውን የካርቨር የትምህርት አገልግሎቶች ማእከል ግቢ ሞልተውት ነበር።

ወላጆች ከMCPS ሰራተኞች ለመገናኘት፣ ስለ ትም/ቤቱ  ስርአት ፕሮግራሞችና ግብረቶች ለመማር፣ እና ስለ ማህበረሰቡ መገልገያዎች መረጃ ለመቅሰም እድል ነበራቸው። በበአሉ አይነተኛ ክውነቶች የተካተቱት በተማሪዎችና በማህበረሰብ ቡድኖች የቀረቡ ትርእይቶች፣ ነፃ የጤና ምርመራዎች፣ እና ለልጆች መደሰቻዎችና ግጥሚያዎች ትኩረት የተደረገባቸውን (ቪድዮ ይመልከቱ)። ተማሪዎች የአዲሱን የትምህርት አመት ጉጉታችውን ከMCPS ቲቪ ጋር ለመጋራት እድል ነበራቸው፣ የቪድዮ መልእክቶቻቸውን እዚህ ቃኙዋቸው።

የMontgomery County ቢዚነሶች፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ እና ግለሰቦች ምስጋና ይግባቸው፣ MCPS እገዛ ለሚገባቸው ተማሪዎች በሚያስፈልጓቸው አቅርቦቶች የተሞሉ 20,000 የጀርባ ቦርሳዎች መግዣ Give BACKpacks በተባለው ዘመቻ በቂ ገንዘብ ለማሰባሰብ ችሏል።

የጀርባ ቦርሳዎቹ ለስርጭት ወድያውኑ ወደ 51 ት/ቤቶች በቀጥታ ተልከዋል።

የMCPSን ወቅት በመጀመርያው የት/ቤት ቀን ተመልከቱ

**እለቱን ያስታውሱ! ሶስተኛው አመታዊ የት/ቤቶች ይዞታ ቀን ለኖቨምበር 11 ተቀጠረ**

Superintendent Joshua Starr ሶስተኛውን አመታዊ የት/ቤቶች ይዞታ ዲስኩር በስትራትሙር የሙዚቃ ማእከል ማክሰኞ፣ ኖቨምበር 11 ያቀርባል።  ክውነቱ ነፃ ነው በMCPS ተማሪዎች የሚቀርቡ ትርእይቶችና የኪነት ስራዎችም ይኖራሉ። በክውነቱ፣ Dr. Starr ተማሪዎችን እንዴት ለወደፊቶቻቸው ስኬት ልናዘጋጃቸው እንደምንችል ራእዩን ያጋራል እናም የጎበዞች ተማሪዎቻችንና ሰራተኞቻችንን ስኬቶች ላይ ላዩን ይገልፃል።

ለተጨማሪ መረጃዎችና ስለክውነቱ መልስ ለመስጠት፣ www.mcpsstateoftheschools.org ይጎብኙ።

**አዲስ በዚህ አመት፡ ሪሳይክል መሆን የሚችሉ የምሳ ስሀኖች**

የMCPS ለሃለፊነት ያለው የአካባቢ እንክብካቤ ግዴታ የገባበት ዘመን 35 አመቶች በላይ ዘልቋል፣ ቀድሞ ከ1970ዎቹ የመጀመርያው የሀይል መመርያ እና ፕሮግራም ቅርፅ ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ።

በዚያን ወቅት፣ MCPS በተፈጥሮ አቀባ (sustainability) እና በአካባቢ እንክብካቤ ሀገራዊ መሪ ሆኗል። ዲስትርክቱ ፣ ከዩ. ኤስ. የትምህርት መምርያ የ2013 የዲስትሪክት የተፈጥሮ እንክብካቤ ሽልማት (District Sustainability Award) እና አራት ብሄራዊ አረንጓዴ ሪበን ት/ቤት (National Green Ribbon School) ሽልማቶች  የሚያካትት በርካታ ሽልማቶች ለተፈጥሮ አቀባ ላለው ፅናት አሸንፏል።

MCPS በዚህ አመት ወደ ሪሳይክልድ የምሳ ሰሀኖች በሁሉም ት/ቤቶች በመንቀሳቀስ የአካባቢ እንክብካቤ ጥረቶችን እያስፋፋ ነው። አዲስ ሪሳይክልኤብል የምሳ ሰሀኖች የፖሊስቲሪን ሰሀኖች ይተካሉ። ባለፈው ጊዜ፣ ወደ ሪሳይክልድ የወረቀት ሰሀኖች የመቀየር ዋጋ እጅግ በጣም ውድ

ነበር። ቢሆንም፣ የMCPS የምግብና የአመጋገብ ስነፍልጠት አገልግሎቶች (Division of Food and Nutrition Services) ክፍል ከፍተኛ ጥራት ያላቸው፣ ርካሽ ስሀኖች ለመለየት ከአምራቾች እና ከሌሎች ሀገር-አቀፍ የት/ቤት ዲስትሪክቶች ጋር ተባብሯል።

የMCPS የት/ቤት ሀይልና ሪሳይክሊንግ ቡድን ከሁሉም የMCPS ት/ቤቶች ጋር በመሆን ስሀኖች በሚገባ ሪሳይክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ እየሰራ ነው።

[ስለ የMCPS አካባቢያዊ የተፈጥሮ እንክብካቤ ይማሩ]

## አዲስ የስነምግባር ህግ ለMCPS ተማሪዎች

ሰላማዊ፣ ምርታማ፣ እና አወንታዊ የትምህርት አካባቢ ለማረጋገጥ፣ Montgomery County Public Schools (MCPS) ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ እና ሰራተኞች የት/ቤት ህጎችንና ደንቦችን መገንዘብ ለማገዝ ሁለት ሰነዶች ያትማል፤ ከተማሪ የሚጠበቁ ስነምግባር፤ እና ህጎችን በመጣስ ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ ቅጣቶች።

**የአንድ ተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች መመርያ ተማሪዎች** በMCPS የሚደሰቱባቸው መብቶችና ሀላፊነቶች አጭር መግለጫና በተማሪዎች ላይ ተፅእኖ ያላቸው ህጎችና ሀላፊነቶች ማጠቃለያ ነው።

**የMCPS የስነምግባር ህግ** ለ2014-2015 የትምህርት አመት አዲስ ህትመት ነው። የስነምግባር ህጉ የቅደም ተከተሎችና መመርያዎች እንዲሁም የተለያዩ መመርያዎችን፣ ደንቦች፣ እና ህጎች በመጣሳቸው ተማሪዎች ሊገጥሟቸው የሚችሉ የቅጣት አይነቶች አጭር መግለጫ ይሰጣል። መመርያው በተጨማሪ የMCPS የዲሲፕሊን ፍልስፍናን ይተችበታል እናም የተለያዩ የዲሲፕሊን ግብረመልሶችን ፍቺ ይሰጣል።

ሁሉም የMCPS ቤተሰቦች የነዚህ ሰነዶች አንዳንድ ቅጂ በየት/ቤታቸው ይሰጣቸዋል። ወላጆች እና አሳዳጊዎች መብቶችና ሀላፊነቶች እና ዲስትሪክቱ ከስነምግባር የሚጠብቃቸውን ለመገንዘብ እንዲችሉ ሰነዱን ከተማሪያቸው ጋር ድህረ እይታ እንዲያደርጉበት ይበረታታሉ። ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባካችሁን የት/ቤታችሁን አስተዳዳሪ ጠይቁ።

[በተጨማሪ ይማሩ]

## የት/ቤቶቻችንን ፅጥታ በማክበር አግዙ

ማንም ሰው ለሰላማዊና ጤናማ የት/ቤት አካባቢ ማበርከት ይችላል። አብዛኛውን ግዜ፣ የወላጆችና የተማሪዎች ጥቆማዎች የወጣቶች ሁከት፣ የእፅና ያልኮል ብልሽት፣ የወንበዴ ተሳትፎ እና ከሌሎች የተማሪዎች ደህንነት አደጋዎች ለመከላከል ያስችላሉ። MCPS ዛቻዎች፣ ወይም የደህንነትና የፀጥታ ሁከቶች ማመልከቻ ምስጢራዊ Safe Schools Hotline (አስተማማኝ

ት/ቤቶች ልዩ መስመር) መገናኛ አሉት። 301-517-5995 በቀን 24 ሰአት/በሳምንት ሰባት ቀኖች መደወል ይችላሉ። አንድ አጠራጣሪ ነገር አይተው እና/ወይም ሰምተው ለማሳወቅ የሚፈልጉ ተማሪዎች በ274637 (CRIMES) የጥቆማ ቴክስት Text-a-Tip ማድረግ ይችላሉ።

ወላጆች ስለMCPS የደህንነት ቅደም ተከተሎች በSafety and Security ድረገፅ በመጎብኘት እንዲማሩ እናሳስባለን። በቦታው የሚገኙ ቪድዮዎች በlockdown (ዝጋ)፣ shelter in place (መጠለያ ቦታ) እና evacuation (ለቀህ ውጣ) የሚያካትቱ ስለ ትም/ቤት ፀጥታ ሂደቶችና ፕሮቶኮሎች ያብራራሉ። ስለ ኮምፒውተር ደህንነት (cybersecurity)፣ አስቸኳይ ሁኔታ ዝግጁነት እና ስለሌላም ሌላም መረጃም በተጨማሪ አለ።

በት/ቤት ንብረት ውስጥ፣ በት/ቤት አውቶብስ፣ ወይም ት/ቤት ስፖንሶር በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚደርሱ አቅመቢስ ላይ መደንፋት (bullying)፣ ማስጨነቅ እና የማስፈራራት ተግባሮች ተማሪዎችና ወላጆች እንዲያሳውቁት MCPS ያበረታታል። ቡሊዪንግ (bullying) የቃል፣ አካላዊ ወይም የፅሁፍ (ኤሌክትሮኒክን ጨምሮ) ሊሆን ይችላል እናም በተማሪዎች፣ ወላጆች ፣ የቅርብ አዋቂ ዘመዶች እና  የት/ቤት ሰራተኛ አባሎች ሊዘገቡ ይችላል። ለርእሰ መምህሩ/ሯ ገቢ የሚደረጉት ዘገባዎች በBullying, Harassment or Intimidation Reporting Form ላይ  ተሞልቶ ይቻላል።

## ስለ ኮንሶርሺያ እና ልዩ የማመልከቻ ፕሮግራሞች ይበልጥ ይማሩ

የNortheast (NEC) እና የDowncounty (DCC) ኮንሶርሻዎች እና የከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት የማመልከቻ ፕሮግራሞች የመረጃ ስብሰባዎች በሰፕተምበር እና በኦክቶበር ያካሂዳሉ። NEC ወይም DCC የሚኖሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ስለ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አማራጮች፣ ኮንሶርሻ ት/ቤቶች፡ የChoice ሂደትና ልዩ የማመልከቻ ፕሮግራሞች መረጃዎች ያገኛሉ። ማመልከቻዎች በሰፕቴምበር መጨረሻ ላይ በት/ቤቶችና በMCPS ድረገፅ ይገኛሉ።

በኤሌሜንታሪ የከፍተኛ ተስጥኦ ማእከሎች ለመማር የሚፈልጉ የ3ኛ ክፍል ተማሪ ቤተሰቦች በኦክቶበር ወር የመረጃ ስብሰባዎች ተዘጋጅተዋል። ማመልከቻዎች ወደየቤታችሁ በሰፕቴምበር ወር በፖስታ ይላካሉ በድረ ገፁም እንዲገኙ ይደረጋል። በመካከለኛ ትም/ቤት ማግኔት ኮንሶርሺየምና የመካከለኛ ት/ቤት ማመልከቻ ፕሮግራሞች ለመማር ፍላጎት ላላቸው የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችና ወላጆቻቸው የሚሆኑ የመግለጫ ስብሰባዎች በሰፕቴምበርና በኦክቶበር በፕሮግራም ተይዘዋል። ማመልከቻዎች በሰፕቴምበር መጨርሻ ላይ በት/ቤቶችና በMCPS ድረገፅ ይገኛሉ።

## MCPS በዜናዎች

ጥቂት ትርፍ ደቂቃዎች አለዎትን? እንግዲያስ ስለMCPS ወቅታዊ ርእሰ አንቀፆች፣ ቪድዮዎች እና የጋዜጣ መግለጫዎችን ይከታተሉ።

### ቪድዮዎች

Welcome Back Students!
አስገራሚ ቀን በMCPS ወደ-ት/ቤት-መመለስ በአል
ለት/ቤት ዝግጁ ነን!—በMCPS ውስጥ በሰመር የሚካሄደውን ስራ ሁሉ ይመልከቱ
የት/ቤቶች መክፈቻ ቀን ዲስኩር በSuperintendent ሰራትኛ እና በቦርድ ፕረዝደንት Kauffman (ካውፍማን)
አዳዲስ መምህራን ከMCPS ጋር ተዋወቁ

### MCPS በዜናዎች

በMontgomery አዲስ የትምህርት አመት ይጀምራል
አዲስ የትምህርት አመት በMontgomery ከአዳዲስ መነሳሻዎችና ከተጠበቀው ምዝገባ ጋር ተጀመረ
አመታዊ የወደ-ት/ቤት-መመለስ በአል ደስታን፣ መረጃንና መልካም ጤናን አጠቃሏል
የመጀምርያው የትምህርት ቀን 202ኛውን ት/ቤት ወደ Montgomery ያመጣዋል
MCPS የተመዝጋቢዎች ቁጥር ክብረወሰን ያስተናግዳል
የስነምግባር ህግ በMontgomery Co. ት/ቤት ለውጦች መካከል

### የጋዜጣ መግለጫዎች

የትምህርት ቦርድ በተማሪ ዲሲፕሊን መመርያ በቀረቡት ክለሳዎች ላይ ህዝባዊ አስተያየት ይሻል
የMCPS ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ተመልሰው አመሩ
የ ወደ-ት/ቤት-መመለስ በአልን በሺዎች የሚቆጠሩ ተከታተሉ
Beverly Farms ES Gold LEED Certification አገኘ
ለMCPS ተመራቂዎች ACT አፈፃፀም ተሻሻለ

### ሌሎች ታሪኮች

Maria Navarro (ማርያ ናቫሮ)፣ የMCPS ዋና የአካዴሚ መኮንንን ይገናኙ
ከSean McGee (ሻን ማ'ጊ)፣ የWilson Wims Elementary School አዲሱ ርእሰ መምህር ጋር አምስት ጥያቄዎች

**ያውቁ ነበር ወይ?**

MCPS አሁን 25 ሚልዮን square feet የሚደርስ የህንፃ ወለል—427 የፉትቦል ሜዳዎች የሚያክሉ አለው!

በዚህ ሰመር፣ MCPS ት/ቤቶችን 1.2 ሚልዮን እርሳሶች ከዝኖባቸዋል—ከጫፍ ወደ ጫፍ ተሰልፈው፣ ከዲ.ሲ. እስከ ፊሊ ሊደርሱ የሚችሉ እርሳሶች።